እንዳይጠናከር ሲያደርጉ የነበረውን ጥረት በበለጠ ለማሳካት ጥሩ ዕድል እንዳገኙ በመተማመን በኢዴአፓ-መድህን ላይ የጥቃት እጃቸውን አበረቱ፡፡

በዚያ በኢዴአፓ-መድህን ላይ ከሁሉም አቅጣጫ የጥቃት ዘመቻ በበረታበት ወቅት ፓርቲያችን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሰጣቸው መግለጫዎች ከቅንጅቱ አመራር ጋር የነበረው ልዩነት በመጨረሻ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ያለውን ግምት ለጊዜና ለታሪክ ፍርድ በሚከተለው አባባል አስቀምጦ ነበር ያለፈው፡፡ ይኸውም -

‹‹አሁን ውሽትና አሱባልታ ቦታ ባገኙበት ወቅት እውነት ተናግሮ ማሳመን ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን የማን አቋም ትክክል እንደሆነ የገባንበት ሂደት በቅርብ ጊዜ እራሱ ስለሚመሰክር እሱን መጠበቅ ይሻላል፡፡ አሁን የቅንጅቱ መሪዎች እየሄዱበት ባለው አቅጣጫ የቅንጅቱን ህልውና አስጠብቀው ከቀጠሉና የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል በአግባቡ መምራት ከቻሉ እኛ በአሁኑ ወቅት የደረስንበት አቋምና ውሳኔ ስህተት ስለሚሆን ያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአደባባይ ወጥተን በድፍረት ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡ ካስፈለገም ከትግሉ ሜዳ ራሳችንን እናገላለን፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የቅንጅቱ መሪዎች አሁን በሄዱበት መንገድ ያሰቡት ሳይሳካ ቀርቶ የቅንጅቱን ህልውናና የሕዝቡን የሠላማዊ ትግል ሂደት አደገኛ አጣብቂኝ ውስጥ ካስገቡትም ለአጠፋት ጥፋት ተጠያቂ መሆንና ይቅርታም መጠየቅ ያለባቸው እነሱ ይሆናሉ›› የሚል ነበር፡፡

ማን ትክክል እንደነበርና ማን ተሳስቶ እንደነበር ዛሬ የትግሉ ሂደትና ጊዜ እየመሰከረልን ነው፡፡ ፓርቲያችን በቅንጅቱ ውስጥ በነበረበት ጊዜም ሆነ ከቅንጅቱ ከወጣ በኋላ የተከራከረላቸውና ውድ ዋጋ የከፈሉባቸው አስተሳሰቦችም ትክክል እንደነበሩ በግልፅ እየታየ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ከቅንጅቱ ለመውጣት የተገደደበት ምክንያት ምን ያህል ተገቢ እንደነበረና ፓርቲያችን ከቅንጅቱ ራሱን በማግለሉ ብቻ የደረሰበት ጥቃትና ውንጀላ ምን ያህል የተሳሳተ እንደነበር ጊዜና ሂደት እያረጋገጠ ይገኛል፡፡ ኢዴአፓ-መድህን ከመጀመሪያው የዚህ ዓይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ካላቸው ኃይሎች ጋር ያለ በቂ ጥንቃቄ አብሮ ለመስራት መሞከሩና በኋላም ላይ ችግሮች መፈጠር ሲጀምሩ ቀደም ብሎ እራሱን ከቅንጅት መነጠል አለመቻሉ ስህተት እንደነበር አምኖ ተቀብሏል፡፡ ነገር ግን ከቅንጅት ጋር ተያይዞ በሚነሱና የኢትዮጵያን ሕዝብ የዲሞክራሲ ትግል በብዙ አጥፍ ወደኋላ ከመሰሱ ጉዳዮች እንዳር በየትኛውም የልዩነት ነጥብ ላይ ኢዴአፓ-መድህንን ጥፋተኛ ማድረግ የማይቻል መሆኑን አሁንም አፅኖት ሰጥቶ መግለፅ ለፓርቲያችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከእጃችን ሾልኮ ላመለጠው የትግል ውጤትና በሕዝቡ ላይ ለደረሰው የሞራል ድቀት ለውድቀቱና ለውርደቱ ሁሉ ተጠያቂዎቹ በቅርቡ ሕዝብንና መንግሥትን ይቅርታ ጠይቀው ከእስር ቤት የተፈቱትና አሁንም የተለያየ አንፃ ፈጥረው በመሻኮት ላይ ያሉት የቅንጅት ቁንጮ አመራሮች ናቸው፡፡

በወቅቱ ኢዴአፓ-መድህን ይህ የቅንጅት አመራር የትግላችንን ውጤት የሚያስነጥቅ፣ አገሪቱንም ለአደጋ የሚያጋልጥ፣ በኢትዮጵያ ሥርዓታዊ ለውጥ ለማምጣት የተፈጠረውን ተስፋ የሚያጨልምና በአጠቃላይም በቅንጅት የተያዘው አቅጣጫ የድርጅቱን ሕልውና ማጣትና የመሪዎችን መታሰር አስከትሎ የትግሉን ዋነኛ ጥያቄ ወደ እስረኛ የማስፈታት አጀንዳ አንክታክቶ የሚያወርድ ይሆናል ብሎ ተከራክሮ ነበር፡፡ ታዲያ ባለፉት ሁለት ዓመታት የሆነው ይህ አልነበረምን? ዛሬ የቅንጅቱ ትግል ከዚህ ደረጃም ወርዶ በገንዘብና በሥልጣን ጥቅም መሻኮት ሆኗል፡፡ ማነው ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ?

ባለፉት ሁለት ዓመታት በምርጫው ሂደት በቅንጅት ሥር ተሰልፎ ወደ ዲሞክራሲያዊ ትግል የገባው ሕዝብ "እኔ ነኝ ቅንጅት" "እኔ ነኝ ቅንጅት" በመባባል በሌለ ሥልጣን ወራሽነት በመወዛገብ ላይ ካሉ የተለያዩ ቡድኖች እንዱን ከሌላው ለመለየት ተቸግሮ ይገኛል፡፡ ኢዴአፓ-መድህን ገና ከሁለት ዓመት በፊት አበክሮ ያስጠነቀቀው ይህ እንዳይሆን አልነበረምን? የቅንጅት አባል ድርጅቶች አባል የሆነው፣ ለቅንጅት የምርጫ ታዛቢ በመሆን የሰራው፣ ቅንጅትን የደገፈውና ድምፁን ለቅንጅቱ የሰጠው ሕዝብ ባለፉት ሁለት ዓመታት ምን ሲደርስበት ነበር? ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማነው?

በርግጥ በቅርቡ ኢሕአዴግንና ሕዝብን ይቅርታ ጠይቆ ከእስር የተፈታው የቅንጅት አመራር ከሃያ ወራት ቆይታ በኋላ ሁሉም ነገር ገብቶት፣ መሳሳቱን አምኖ ለጥፋቱ ሁሉ ራሱን ተጠያቂ አድርጓል፡፡ የዚህ አመራር አባላት የሆኑ ሰዎች በዚያ ከፍተኛ የሕዝብ መሪነት ስብዕናና የሞራል ኃላፊነት ደረጃ መንግሥትንም ሆነ ሕዝቡን ያታልላሉ ብለን ስለማናምን አጥፍተናል ብለው የፈረሙት በርግጥም ጥፋታቸውን ከልባቸው ተረድተው ነው ብለን እንገምታለን፡፡ ይህ አመራር ከነበረው ጠባብ ምርጫ

☎ 0115-508727 0114655765 ✉ 1Ø1458
0115-508728

ፍትሕ ሕርኅጋፍ የበገኔ ሃዘብ ሕጥር ፅ/ር 145